AMHARIC

ALEXANDRIA CITY PUBLIC SCHOOLS ~ SCHOOL NUTRITION SERVICES
1340 Braddock Place, Alexandria, Virginia 22314

2021 - 2022 INSTRUCTIONS FOR COMPLETING THE HOUSEHOLD APPLICATION FOR FREE AND REDUCED-PRICE MEALS

የተከበሩ ወላጅ/ አሳዳጊ፤

የ2021-2022 በቀጥታ የማሳወቂያ ደብዳቤ ካልተገለጸልዎት በስተቀር በየዓመቱ አዲስ የትምህርት ዘመን አዲስ የማመልከቻ ቅፅ መሞላት ይኖርበታል። ለመላው የእርስዎ ቤተሰብ መሞላት የሚኖርበት አንድ ማመልከቻ ብቻ ነው።

እባክዎን ቅፁን ሲሞሉ በእስክሪፕቶ ይሙሉ (እርሳስ አይጠቀሙ)። እንዲሁም እንደሚታይ አድርገው ይሙሉ።

የነፃ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ ምግብ ለማግኘት የማመልከቻ ቅጽን ለመሙላት እነዚህን መመሪያዎች እባክዎን ይከተሉ። በአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ልጅዎ (ልጆችዎ) ከአንድ ቫ/ቤት በላይ የሚከታተሉ ቢሆንም ሊሞሉ የሚገባዎ ቅፅ አንድ ብቻ ነው። ልጅዎ ለነፃ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ ምግብ የማግኘት መቻሉን ለማረጋገጥ ቅፁን በሙሉ ይምሉ። እያንዳንዱ ደረጃ በደረጃ የቀረበው መመሪያ በቅጹ ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው። በማንኛውም ጊዜ ቅፁን ሲሞሉ እርግጠኛ ካልሆኑ እባክዎን ሶኒያ ግራንት (Sonya Grant) በስልክ **703-619-8048** ያግኙ፤ food@acps.k12.va.us

የሚቀርበው የምግብ ዓይነቶች በሙሉ የአሜሪካን የግብርና ዲፓርትመንት መስፈርት ያሞሉ መሆን አለባቸው። አንድ ልጅ በዶክተር የአካል ጉዳተኛ እንደሆነ ከተወሰነ እንዲሁም ጉዳቱ በመደበኛነት የሚዘጋጀውን ምግብ ለመብላት የሚያስቸግረው ከሆነ ትምህርት ቤቱ በዶክተሩ የሚታዘዘውን ምትክ የምግብ ዓይነት ያዘጋጃል። ምትክ የምግብ ዓይነት ማዘጋጀት የሚያስፈልግ ከሆነ ምንም ተጨማሪ ክፍያ አይጠየቅም። ተማሪዎ በጉዳት ምክንያት ምትክ አማራጭ የምግብ ዓይነት የሚያስፈልገው ከሆነ እባክዎን ከ **Cynthia Hormel ጋር በ 703-619-8048 ይገናኙ**። ተጨማሪ የተመጣጠነ የምግብ ድጋፍ (SNAP) ወይም ጊዜያዊ እርዳታ ድጋፍ ለሚሹ ቤተሰቦች (TANF) የሚያገኙ ቤተሰቦች ውስጥ የሚኖሩ ልጆች ነፃ የትምህርት ቤት ምግብ ማግኘት ይችላሉ። በማደጉ ማዕከላት ወይም በፍርድ ቤት ኋላፊነት ያሉ የማደጉ ልጆች ነፃ ትምህርት ቤት ምግብ ማግኘት ይችላሉ። ለሜዲክ ኤይድ ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ለነፃ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ ምግብ የማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በተለይ ለእናቶች የሚጠገውን ልዩ የተመጣጠነ የምግብ ድጋፍ (WIC) የሚያገኙ ቤተሰቦች ልጆች ለነፃ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ ምግብ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የቤተሰብዎ ገቢ በፌደራል የገቢ መጠን መለኪያ ካለው መመሪያ እኩል ወይም ከዚያ በታች ሆኖ ከተገኘ ልጆች ለነፃ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ ምግብ የማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ***የልጆችዎ ያለፈው ዓመት ማመልከቻ ለአዲሱ የትምህርት ዓመት ለመጀመሪያ ጥቂት ቀናት ብቻ ነው የሚያገለግለው ።***

የኮሚዩኒቲ ብቁነት ደንብ (Community Eligibility Provision (CEP))

ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ቤተሰቦች ሌሎች ሌሎች የኤሲፒኤስ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ልጆች ከሌላቸው በስተቀር የነፃ እና የቅናሽ ዋጋ ምግብ ማመልከቻ ማጠናቀቅ አያስፈልጋቸውም። የሚከተሉት ትምህርት ቤቶች በሲኢፒ አቅርቦት ላይ የሚሳተፉ ሲሆን ቁርስ እና ምሳ በምንም ክፍያ ለተማሪዎች ይሰጣሉ

Cora Kelly Elementary
Ferdinand T. Day Elementary
James K. Polk Elementary
John Adams Elementary/Early Childhood
Samuel Tucker Elementary
William Ramsay Elementary
Jefferson Houston PreK-8
Patrick Henry K-8
Francis C. Hammond Middle

ደረጃ 1፤ ሁሉንም የቤተሰብ አባላት ከህፃን ጀምሮ፣ ልጆችና እስከ 12ኛ ክፍል የደረሱ ተማሪዎች በሙሉ ስም ዝርዝር ፃፍ።

በቤተሰብዎ የሚኖሩ ህፃናት፣ ልጆችና ለትምህርት የደረሱ ልጆችን ስም ፃፍ። የቤተሰብ አባል ለመሆን የግድ ዘመድ መሆን የለባቸውም።

- እድሚያቸው 18 ወይም ከዚያ በታች ሆኖ በቤተሰብ ገቢ ድጋፍ የሚያገኙ፣ በአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚከታተሉ ተማሪዎች እድሚያቸው ሳይታይ።
- በጊዲፈቻ ስርዓት በእርስዎ እንክብካቤ ያሉ ወይም መኖሪያ ቤት የሌላቸው፣ ስደተኞች ወይም ከቤት የጠፉ ወጣቶች ፣

የልጅዎን የተማሪ መታወቂያ ቁጥር የሚያውቁት ከሆነ በእያንዳንዱ ሣጥን ውስጥ ቁጥሩን ይፃፉ።	የእያንዳንዱን ልጅ ስም ፃፍ። በትምህርት ቤት የተመዘገበውን የእያንዳንዱን ልጅ ስም ፃፍ። *የቤት ቅፅል ስም አትጠቀሙ።*	የእያንዳንዱን ልጅ የትውልድ ቀን ፃፍ፤ በእያንዳንዱ ሣጥን ውስጥ የልጁን የትውልድ ቀን/ ወር / ቀን/ ዓመት በቁጥር ፃፍ።	ልጅዎ ወደ የትኛው ት/ቤት ይሄዳል/ትሄዳለች ስንተኛ ክፍል ነው/ናት? የእያንዳንዱን ተማሪ የክፍል ደረጃና "ክፍል" በሚለው መስመር ፃፍ የትምህርት ቤቱን ኮድ በቀጠዩ መስመር ፃፍ።	የማደጉ ልጅ አለዎት? ስማቸው እዚህ የተፃፈው ልጆች በማደጉ ማዕከላት ወይም በፍርድ ቤት የኋላፊነት ያሉ ከሆኑ ማደጉ ("Foster Child") የሚለውን ለማመልከት 'F' በሚል ርእስ ያለውን ምልክት አድርጉ። የሚያመለክቱት ለማደጉ ልጅ ብቻ ከሆነ ደረጃ 1 ከአጠናቀቁ በኋላ ወደ **ደረጃ 4** ይቀጥሉ።
ልጅዎ ለትምህርት ቤቱ ክልል አዲስ ከሆነ ከተማሪው ስም ጐን ምልክት አድረጉ።	**በማመልከቻው ካለው መስመር ቁጥር በላይ ልጆች ካሉ ለተጨማሪ ልጆች የሚያስፈልገው መረጃ የያዘ ሁለተኛ ገፅ ማያያዝ ይቻላል።**	ለምሳሌ፤ *የልጁ የትውልድ ቀን ጃንዋሪ 31 ቀን 2009 ነው።* ወ ወ ቀ ቀ አመ አመ: 0 1 3 1 0 9	ለምሳሌ፤ *ልጁ በ2ን አዳማስ የ2ኛ ክፍል ነው።* የክፍል ደረጃ፤: 0 2 የትምህርት ቤቱ ኮድ፤: J A	ከእርስዎ ጋር የሚኖር የማደጉ ልጅ እንደ እርስዎ የቤተሰብ አባል ስለሚቆጠር በማመልከቻ ቅፁ ውስጥ መካተት ይኖርበታል። የማያመለክቱት ለማደጉና የማደጉ ላልሆኑ ልጆች ከሆነ ወደ **ደረጃ 3** ይቀጥሉ። **ቤት የሌላቸው፣ ስደተኞች ወይም ከቤት የጠፉ ልጆች አሉ?** በዚህ ክፍል ውስጥ ስምአቸው የተጠቀሰው አላይ የተጠቀሰውን የሚማሉ ከሆነ ከልጁ/ከልጅም ስም ቀጥሎ "ቤት የሌላቸው፣ ስደተኞች ወይም ከቤት የጠፉ" በሚለው ላይ ይሞላ እና **ሁሉንም የማመልከቻ ክፍል ደረጃ በደረጃ ይምሉ።** ለተጨማሪ መረጃ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ቤት የሌላቸው/የማደጎ አገልግሎት አስተባባሪ **Rhaea Goff** በስልክ 703-619-8071 ያግኙ።

ደረጃ 2፤ በ SNAP ወይም TANF ፕሮግራም ተሳታፊ የሆነ ቤተሰብ አባል አለዎት?

በቤተሰብዎ (እርስዎን ጨምሮ) በሚከተሉት በአንድ ወይም ከዚያ በላይ ፕሮግራሞች የሚሳተፍ ካሉ ልጆችዎ የነጻ የትምህርት ቤት ምግብ ለማግኘት ብቁ ናቸው።

- ተጨማሪ የተመጣጠነ የምግብ ድጋፍ (SNAP)
- ድጋፍ ለሚሹ ቤተሰቦች (TANF) ጊዚያዊ እርዳታ

ከቤተሰብዎ ውስጥ አንድም ሰው እላይ በተጠቀሱት ፕሮግራሞች ተሳታፊ ካልሆነ ፤	በቤተሰብዎ ውስጥ ያሉ እላይ በተጠቀሱት በአንደኛው ፕሮግራሞች የሚሳተፉ ከሆነ ፤
• ደረጃ 2 ክፍት በመተው ወደ ደረጃ 3 ይቀጥሉ።	• ለSNAP ወይም TANF የሚሰጠውን ከ 7-12 የሚደርስ ቁጥር ይፃፉ ከዚያም ወደ ደረጃ 4 ይቀጥሉ። አንድ ቁጥር ብቻ ነው መፃፍ የሚያስፈልገው። የኢ.ቢ.ቲ ካርድ ቁጥር አትጠቀም። በእነዚህ ፕሮግራም ተሳታፊ ሆነው ቁጥሩን የማያውቁት ከሆነ የእርስዎን ጉዳይ የሚከታተልሎትን ወይም የአሌክሳንደሪያ የኮሚዩኒቲና ህዩመን ሰርቪስ በስልክ 703 -746-5700 ያግኙ።

ደረጃ 3፤ የሁሉም የቤተሰብ አባላት ገቢ

ከታች ያለውን የገቢ መመሪያ ይከተሉ ወይም ለተጨማሪ መረጃ በስልክ 703-619-8048 ይጠይቁ። የሚመለከትዎ ከሆነ ልጆችዎ የሚያገኙትንም ገቢ ሪፖርት ይደረግ።

የፌደራል የገቢ መመሪያ፤ የቤተሰብ ገቢዎ ከፌደራል የገቢ መመሪያ በታች ከሆነ ልጅዎ (ልጆችዎ) በነፃ ወይም በዝቅተኛ ዎጋ የትምህርት ቤት ምግብ ሊያገኙ ይችላሉ።

በነፃ ወይም በዝቅተኛ ዎጋ የትምህርት ቤት ምግብ ለማግኘት የገቢ ሠንጠረዥ

ከጁላይ 1 ቀን 2021 እስከ ጁን 30 ቀን 2022 ድረስ በስራ የዋለ

የቤተሰብ ብዛት	አመታዊ	ወርሃዊ (12pp*)	በወር ሁለት ጊዜ (24pp)	በየሁለት ሣምንቱ (26pp)	ሣምንታዊ (52pp*)
1	$23,828	$1,986	$ 993	$ 917	$ 459
2	$32,227	$2,686	$1,343	$1,240	$ 620
3	$40,626	$3,386	$1,693	$1,563	$ 782
4	$49,025	$4,086	$2,043	$1,886	$ 943
5	$57,424	$4,786	$2,393	$2,209	$1,105
6	$65,823	$5,486	$2,743	$2,532	$1,266
7	$74,222	$6,186	$3,093	$2,855	$1,428
8	$82,621	$6,886	$3,443	$3,178	$1,589
ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የቤተሰብ አባል የሚከተለውን ይጨምሩ፤	+ 8,399	+ 700	+ 350	+ 324	+ 162

*pp = ማለት በዓመት ውስጥ የደመወዝ ክፍያ ጊዜ ነው።

የገቢ ደንብ ክፍል፤ *ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በውሩ የሚያገኘውን እያንዳንዱን ገቢ ዓይነት ዘርዝር። በምን ያህል ጊዜ ገቢው እንደሚገኝ ፤- በየሣምንቱ፣ በየሁለት ሣምንቱ፣ በወር ሁለት ጊዜ ወይም በየወሩ። ገቢው የሚመለከት ወደ ቤት የሚወስዱትን የተጣራውን ሳይሆን አጠቃላይ ገቢውን ይግለፁ። አጠቃላይ ገቢ ማለት ከታክስና ከሌሎች ቅንሰናሽ በፊት ያለውን ገቢ ነው። በደመወዝ መክፈያ ቼክ ላይ ያገኙታል ወይም አለቃዎ ሊያሳይዎ ይችላል። እንዲሁም የሠራተኞች ካሣ ክፍያ፣ የሥራ አጥ ክፍያ፣ ወይም የሥራ ማቆም ክፍያ የሚቀበሉ ከሆነ አብረው ይገለፁ። ለሌሎች ገቢዎች እያንዳንዱ ሰው ምን ያህል ከእርዳታ፣ የልጅ ማሳደጊያ ፣ ከቀድሞ የትዳር ጐደኛ ክፍያ (አሊሞኒ) ፣ የጡረታ፣ ሶሻል ሴይኩሪቲ፣ የተጨማሪ የኑሮ ድጋፍ(SSI) እና የወታደር አገልግሎት ክፍያ (VA benefits) ይገለፅ። ሌሎች ገቢዎች በሚለው ስር የአካል ጉዳት ክፍያ፣ ከባንክ የቁጠባ ባንክ ክፍያ ፣ ከቤት ውጭ የሚኖሩ ሰዎች በቆሚነት የሚሰጡት የገንዘብ ድጋፍ ፣ የኪራይ ገቢ እና ሌላ ገቢ ይገለፁ። ከSNAP፣ WIC የሚገኝ ገቢ የፌደራል የትምህርት ክፍያ፣ የማደጐ ልጅ ከሚመድበው ተቋም ቤተሰብ የሚቀበለው የማደጐ ክፍያ ማካተት አያስፈልግም። ራሳቸውን ለቀጠሩ ብቻ ከሥራ የተገኘ ገቢ የሚለው ላይ እንደገቢ ሪፖርት የሚደረገው የንግዱ ወይም ግብርናው የስራ ወጪ ከተቀነሰ በኋላ ነው። በወታደር ወደ ግል የተዛወረ የቤት መርሃ ገብር ውስጥ ተሳታፊ ከሆኑ ወይም በጦርነት ቦታ የሚሰጥ ተጨማሪ ክፍያ እንደ ገቢ ማካተት አይኖርበትም:* ***ምንም ገቢ ለሌለው አዎቂ ገቢ በሚለው ክፍል ላይ "0" ተብሎ ይፃፍ። "0" ተብሎ ከተፃፈ ወይም ክፍሉ ላይ ምንም ነገር ካልተፃፈ ምንም ገቢ የሌለ መሆኑን እያሰወቁ ነው። ለልጆች/ተማሪዎች ገቢ ካላቸው ባለው ቦታ ላይ ይግለፁ። ተማሪው ገቢ ከሌለው ገቢ በሚለው ስር ክፍት መተው ይቻላል።***

ደረጃ 4፤ የመገናኛ መረጃ እና የአዎቂ ሰው ፊርማ

ሁሉም የማመልከቻ ቅፆች በቤተሰቡ ባለ አዎቂ መፈረም አለበት። ይህም የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ፈራሚው የቤተሰብ አባል የሚያረጋግጠው ሁሉም መረጃዎች በሙሉ በትክክልና በተሞላ ሁኔታ ሪፖርት መደረጋቸውን ነው። ይህን ክፍል ከመሙላትዎ በፊት እባክዎን ከታች የተገለፀውን የግል ታሪክ በሚስጥር የሚያዝበትንና የሲቭል መብት መግለጫ ማንበብዎን ያረጋግጡ።

ስም ይፃፉ፤ ይፈርሙ፤ የመጨረሻውን የሶሻል ሴይኩሪቲ አራት ቁጥር እና የዛሬውን ቀን ይፃፉ። በማመልከቻው ላይ የሚፈርመውን ሰው ስም ይጻፍ እንዲሁም "እዚህ ይፈረም" በሚለው ስር ስሙ የተፃፈው ሰው ይፈርም። የመጨረሻውን የሶሻል ሴይኩሪቲ አራት ቁጥር (SSN) ይፃፍ። የሶሻል ሴይኩሪቲ ቁጥር (SSN) ከሌለ "ቁጥር ከሌለ እዚህ ምልክት ይደረግ" በሚለው ምልክት ይደረግ።

የመገናኛ መረጃ ይስጡ። የአሁኑን ወቅታዊ አድራሻ መረጃ ካለ በተሰጠው ቦታ ላይ ይፃፍ። የስልክ ቁጥር ወይም ኢሜል መስጠት ግዴታ አይደለም ሆኖም ግን ከእርስዎ ጋር መገናኘት ካስፈለገ በአፋጣኝ ለመገናኘት ይረዳል።

የተሞላውን ቅፅ ለሚከተለው ይላክ፤

ትምህርት ቤት የተመጣጠነ ምግብ አገልግሎት
SCHOOL NUTRITION SERVICES
1340 Braddock Place, Alexandria, VA 22314

ሌሎች ጥቅሞች፤ ልጅዎ ለሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል። የትምህርት ቤት ክልል አስተዳደር የነፃ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ የምግብ ተጠቃሚነት እጩ መሆኑ የያዘ መረጃ ለሜድክ ኤይድ(Medicaid) እና የፋሜስ(FAMIS)መረጃ መስጠት እንደሚችል ህጉ ይፈቅዳል። እነዚህ ፕሮግራሞች የሚያገኙት መረጃ የትኞቹ ልጆች ለነፃ ወይም በዝቅተኛ ክፍያ የጤና ኢንሹራንስ እንዲያገኙ በመለየት በፕሮግራሞቹ እንዲገቡ ለማድረግ ብቻ ይጠቀሙባቸዎል። እኒዚህ ተቋማት የሚያገኙትን መረጃ ለሌላ ማናቸውም ጉዳይ መጠቀም አይችሉም። የሜድክ ኤይድ ወይም የፋሜስ የስራ ኋላፊዎች መረጃ ለማግኘት ከእርስዎ ጋር ሊገናኙ ይችላሉ። ይህን መረጃ ለሜድክ ኤይድ ወይም ለፋሜስ መረጃውን ለማካፈል ለእኛ ፈቃድ መስጠት አያስፈልግዎትም። የእርስዎ ውሳኔ ልጅዎ በነፃና በአነስተኛ ክፍያ ምግብ የማግኘት እጩነቱን ላይ የሚያመጣው ተጽእኖ የለውም። መረጃው ለሌላ እንዳይተላለፍ ከፈለጉ እባክዎትን በተገቢው መልስ መስጫ ሣጥን ላይ ምልክት ያድርጉ። ለሌላ የእርዳታ ፕሮግራም እጩ ሊሆኑ ይችላሉ። የ SNAP ወይም ለሌላ ፕሮግራም ድጋፍ ለማግኘት በአካባቢ የሚገኘውን የማህበራዊ አገልግሎት ቢሮዎች ያግኙ።

የአካዳሚ/የኮሚዩኒቲ አገልግሎቶች፤ በዚህ ሳጥን ላይ ምልክት በማድረግ ለትምህርት ቤት ኋላፊዎች እና ለፕሮግራሞች በአካባቢው ላሉ የጤና እና የትምህርት አገልግሎቶች እንደ ያለከፍያ ፈተና መውሰድ(ቫውቸር)/ስኮላርሽፕ መወሰን፣ የድጋፍ/የማሻሻያ አገልግሎቶች፣ የህክምና /የጥርስ/ የአይን ክሊኒክ የቢጋ/የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች፣ የትምህርት እቃዎች አቅርቦት፣ የስፖርት ክፍያ ፣ የመስክ ጉብኝት፣ የሙዚቃ መሳሪያ መዋስ ወዘተ... የእርስዎን መረጃ ማስተላለፍ እንድንችል ለእኛ ፍቃድ ሰጥተዋል።

ግዴታ ያልሆነ ምርጫ፤ የልጅዎ የዘር ወይም የጐሣ ማንነት መግለጫ

የልጅዎ ዘር ወይም የጐሣ ማንነት በሚመለከት መረጃ እንዲሰጡን እንጠይቃለን። ይህ ክፍል **በፈቃደኝነት** ላይ የተመሰረተ አማራጭ ሲሆን ልጅዎ በነፃና በአነስተኛ ክፍያ ምግብ የማግኘት እጩነቱን ላይ የሚያመጣው ተጽእኖ የለውም።

የሚስጠራዊነት እና የመረጃ አጠቃቀም መግለጫ፤ የትምህርት ቤት ሃላፊዎች በዚህ ማመልከቻ ላይ ያለ መረጃ ልጆዎ በነፃ ወይም በአነስተኛ ክፍያ ምግብ የማግኘት የሚችል መሆኑን እጩነቱን ለመወሰን ይጠቀመባታል። በብሔራዊ የትምህርት ቤት ምግ ህግ እንደተፈቀደው የትምህርት ቤት አስተዳዳር ከልጅ ከልጆች የምግብ ፣ የጤና ወይም የትምህርት ፕሮግራሞች ጋር ለተገናኙ የስራ ኋላፊዎች በፕሮግራሞቹ ተጠቃሚነት ለመወሰን፣ በጀት ለማስመደብ እና/ወይም ውጤቱን ለመገምገም መረጃውን ሊሰጣዉጡ ይችላሉ።

ማረጋገጫ፤ የትምህርት ቤት ኋላፊዎች በትምህርት ዘመኑ በማናቸውም ጊዜ የእርስዎን እጩነቱን ለማረጋገጥ ማጣራት ይችላሉ። የትምህርት ቤት ኋላፊዎች ልጅዎ በነፃ ወይም በአነስተኛ ክፍያ ምግብ ማግኘት የሚገባው መሆኑን ለመወሰን መረጃዎች እንዲልኩላቸው መጠይቅ ይችላሉ።

ፍትሃዊ አቤቱታ መደመጥ፤ ፍትሃዊ አቤቱታ የመደመጥ መብት አለዎት። በትምህርት ቤቱ የተመጣጠነ ምግብ አገልግሎት ባቀረቡት ማመልከቻ ወይም ባቀረቡት ሰነድ ላይ በሰጠው ውሳኔ የማይስማሙ ከሆነ ለትምህርት ቤቱ የተመጣጠነ ምግብ አገልግሎት (SCHOOL NUTRITION SERVICES) ደብዳቤ በመፃፍ ወይም በስልክ **703-619-8048** መደወል ወይም ለሚከተለው ኋላፊ ደብዳቤ መፃፍ ይችላሉ፤ **ዶ/ር አሊሻ ሐርት(Dr. Alicia Hart) ጊዚያዊ የትምህርት ቤቶች ተቆማት እና ስራ ዳይሬክተር፤ 1340 Braddock Place, Alexandria, VA 22314. ስልክ፤ (703) 619-8289**

ተጨማሪ ለመሆን ድጋሚ ማመልከት፤ ልጅዎ በነፃ ወይም በአነስተኛ ክፍያ ምግብ ለማግኘት በማንኛውም ጊዜ በድጋሚ ማመልከት ይችላሉ። በአሁኑ ሰዓት ብቁ መሆን ባይችሉም እንኳን አንድ ለውጥ ሲፈጠር ማለትም የቤተሰብ ገቢ ከቀነሰ፣ የቤተሰብ ብዛት ከጨመረ ፣ ሥራ አጥ ከሆኑ፣ የ SNAP ወይም TANF ለልጆዎ ከወሰዱ በወቅቱ ማመልከቻውን ይመሉቱ። ብሄዶች ሊጠቆሞ ይችላሉ።

ለማመልከት እርዳታ፤ ማመልከቻውን ሲሞሉ ወይም ስለማመልከቻው ማናቸውም ጥያቄ ካለዎት እባክዎን የትምህርት ቤቱን የተመጣጠነ ምግብ አገልግሎት (School Nutrition Services) በስልክ 703-619-8048 ወይም food@acps.k12.va.us ያግኙ።

ምግብ ፖሊሲ፤ ተማሪዎች የመረጡትን ምግብ ለመዝገት በምግብ ሂሳባቸው ላይ ወይም በእጃቸው ምንም ገንዘብ ካልያዙ ምግብ እንዲያገኙ ይፈቀዳል። ተማሪዎች የፈለጉትን ምግብ ዓይነት ማን መምረጥ አይችሉም። የተማሪውን መክፈል አለመቻል በሌሎች እንዳያውቁ የተቻለው ጥረት ይደርጋል። የምግብ አገልግሎቱም በየቀኑ ያልተከፈለውን ምግብ ሂሳብ ለርእሰ መምህሩ ማሳወቅ አለበት። የርእሰ መምህሩ ተወካይ ለወላጆች/አሳዳጊዎች በሚመርጡት ቋንቋ ስለጉዳዩ ያሳውቃል። እስር(10) ምግብ ሂሳብ ከሞላ ርእሰ መምህሩ ለወላጆች/አሳዳጊዎች ደብዳቤ በፖስታ ይልካል። የሚላከው ደብዳቤ ምን ያህል ያልተከፈለ ሂሳብ እንዳለ እና የተማሪውን የምግብ ሂሳብ እዳ እንዴት መክፈል መተካት እንደሚቻል እንዲሁም በነፃ ወይም በአነስተኛ ዋጋ ምግብ ለማግኘት እንዴት መመዝገብ እንደሚቻል መረጃዎችን ያካትታል። በተጨማሪም ርእሰ መምህሩ የትምህርት ቤቱን ድጋፍ ሰጪ አባላት ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር ተገናኝተው ተማሪው በነፃ ወይም በአነስተኛ ዋጋ ምግብ የማግኘት እንዴት እንደሚቻል ስብሰባ እንዲደረግ ይወስላል። በመሆኑም የኤ.ሲ.ፒ.አስ. ልጆችን ለአደጋ ማጋለጥ የሚጠረጠሩ ሁኔታዎችን ሲመለከቱ ለማህበራዊ ጉዳይ አገልግሎት ዲፓርትመንት ሪፖርት ሊያደርግ ይችላል።

- ከሰኢና ጋር፣ ሲንቲያ ሆርሞል (Cynthia Hormel) MM፣RDN፣SNS
  የትምህርት ቤት የተመጣጠነ ምግብ አገልግሎት ዳይሬክተር

የፌደራል የሲቭል መብት ህግ እና የአሜሪካ የግብርና ዲፓርትመንት (USDA) የሲቭል መብቶችና ፖሊሲዎች የዩ አስ ዲ ኤይ፤ የዩ አስ ዲ ኤይ የስራ ክፍሎች፤ ቢሮዎች፤ ሠራተኞች እና ተቋማት የዩ አስ ዲ ኤይ ፕሮግራሞች የሚያስፈጽሙ ወይም በፕሮግራሞቹ የሚሳተፉ በዘር፣በቀለም፣ የትውልድ ስፍራ፣ በጾታ፣ በሐይማኖት፣ የፖሊቲክ እምነት ምክንያት ልዩነት መፍጠር እይፈቀድም ወይም በየዩ አስ ዲ ኤይ በሚካሄድ ፕሮግራሞች በሲቭል መብት የማስከበር እንቅስቃሴ ተሳታፊ በሆኑት ላይ የበቅል እርምጃ መውሰድ እይፈቀድም። ጉዳት ያለው ስለፕሮግራሙ መረጃ ለማግኘት ሌላ የመገቢቢያ እግራጭ የሚፈልግ ሰው (ለምሳሌ ብሬል ወይም ጉላ ያለ ፅሁፍ፣ በቴፕ የተቀዳ፣ ወይም የአሜሪካብ የምልክት ቋንቋ ሌሎችም) የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለመሆን ጎመለከቱበት ተቆም (ኩቴት ወይም የአካባቢ) ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። መስማት የማይችሉ ወይም የተሳናቸው ወይም የመናገር ችግር ያለባቸው በፌደራል የመንኛ አገልግሎት በስልክ (800) 877-8339 አማክኝነት USDA ጋር መገናኘት ይችላሉ። በተጨማሪም የፕሮግራሙ መረጃዎች ከእንግሊዘኛ ቋንቋ በተጨማሪ በሌላ ቋንቋ ሊያገኙ ይችላሉ። ስለፕሮግራሙ ቅሬታ ለማቅረብ USDA Program Discrimination Complaint Form (AD-3027) በኦላይን ይመሉቱ፤ http://www.ascr.usda.gov/complaint_filing_cust.html እና በዩ.ኤስ. ዲ.ኤ. ቢሮ ወይም በዩ.ኤስ. ዲ.ኤ. አድራሻ በፎርሙ የተጠየቀውን መረጃ በደብዳቤው በማካተት መጻፍ ይችላሉ። የቅሬታ ማቅረቢያ ቅፅ ለማግኘት በስልክ (866) 632-9992 ይደውሉ። የተሞላውን ደብዳቤ ለሚከተለው አድራሻ ይላኩ።

(1) ፖስታ፤ U.S. Department of Agriculture
Office of the Assistant Secretary for Civil Rights
1400 Independence Avenue, SW
Washington, D.C. 20250-9410;

(2) ፋክስ፤ (202) 690-7442 ፣ ወይም

(3) ኢሜል፤ program.intake@usda.gov.

ይህ ሁሉንም በእኩልነት የሚያይና እድል የሚሰጥ ተቋም ነው።

የአሌክሳንደሪያ ከተማ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ~ (703) 619-8048; food@acps.k12.va.us

2021 - 2022 በነፃና በአነስተኛ ክፍያ ምግብ አቅርቦት ማመልከቻ ቅጽ

4741

Apply online at **www.schoolcafe.com/alexandriacps**

AMHARIC

ለአንድ ቤተሰብ አንድ ቅጽ ብቻ ሙላ። በጥቁር ወይም ሰማያዊ እስክሪፕቶ በመጠቀም ሙላ (እርሳስ አትጠቀም)።

2021-2022 ትምህርት ዓመት በቀጥታ ከትምህርት ቤቱ የተመጣጠነ ምግብ አገልግሎት ለእያንዳንዱ ልጅ የብቁነት ማረጋገጫ ደብዳቤ ካገኙ ይህን ቅፅ መሙላት **አያስፈልግም።**

ደረጃ 1፤ የቤተሰቡን አባላት ስም ዘርዝር ፤ ህፃናት፣ ልጆች እና ተማሪዎች (ተጨማሪ ቦታ የሚያስፈልግ ከሆነ ሌላ ወረቀት ማያያዝ ትችላለህ።)

የተማሪው መታወቂያ ቁጥር (ካስፈለገ)	ለአሌ.ፐብሊ ኢዲያስ ነህ?	የመጨረሻ ሥም	የመጀመሪያ ስም	መካከለኛ	የትውልድ ቀን	ክፍል	የት/ ቤቱ መለያ ኮድ	F*	H	M	R
		የልጁ ስም 1			ወ ወ ቀ ቀ ዓ ዓ						
		የልጁ ስም 2			ወ ወ ቀ ቀ ዓ ዓ						
		የልጁ ስም 3			ወ ወ ቀ ቀ ዓ ዓ						
		የልጁ ስም 4			ወ ወ ቀ ቀ ዓ ዓ						

የትምህርት ቤቱ መለያ ኮድ - አንደኛ ደረጃ (መምህለ - 5): **CB**=ቻርልስ ባሬት (Charles Barrett); **CK**=ኮራ ኬሊ (Cora Kelly); **DM**=ዳግላስ ማካርተር; **EC**=የቅድመ ልጅነት ማዕከል (Early Childhood Center); **FD**=ፊርዲናድ ዴይ (Ferdinand Day); **GM**=ጆርጅ ሜሰን (George Mason); **JA**=ጀን አዳማስ (John Adams); **JP**=ጀምስ ፖልክ (James Polk); **LC**=ሊይለስ ክሮች (Lyles Crouch); **MV**=ማውንት ቨርነን (Mount Vernon);**MM**=ማቲው ማውሪ (Matthew Maury); **ST**=ሣሙኤል ተከር (Samuel Tucker); **WR**=ዊሊያም ረምሲ (William Ramsay) **መምህለ-8 ት/ቤቶች:** **JH**=ጀፍ ሂውስተን (Jeff Houston); **PH**=ፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry); **ሁለተኛ ደረጃ (ከፍሎች 6-12):** **FH**=ፍራንሲስ ሐመንድ (Francis Hammond); **GW**=ጅዎርጅ ዋሽንግተን(George Washington); **MH**=ሚኒ ሐዋርድ (Minnie Howard); **AC**=ቲሲ ዊሊያም (Alexandria City High)

F = የማደጉ ልጅ
H = የመጠለያ ቤት የሌለው
M = ስደተኞች R = ከቤት የጠፉ

ለማደጉ ልጅ ፡ መጠለያ ለሌላቸው፡ ለስደተኞች ወይም ከቤት ለጠፉ ልጆች ማመልከቻውን የሚሞሉ ከሆነ አግባብነት ያለውን ማጠን ምልክት አድርግ እንዲሁም መጠለያ የሌላቸውን ጉዳይ ከሚከታተሉ የት/ቤት ሰራተኞ ጋር በስልክ ይገናኙ።.

የሚያመለክቱለት ተማሪ በማደጉ ልጅች ተንከባካቢ ተቋም ወይም በፍርድ ቤት ኃላፊነት ስር ያለ **የማደጉ ልጅ** ከሆነ **በሣጥኑ ውስጥ ምልክት በማድረግ ወደ ደረጃ 4 ቀጥል።**

የማደጉ ልጅ ያልሆኑ ሌሎች ልጆች ካሉ **ደረጃ 2**ን ይሞላ ወይም በቤተሰብ ውስጥ SNAP ወይም TANF ተጠቃሚ ካልሆኑ ወደ **ደረጃ 3** ይቀጥሉ።

ደረጃ 2፤ የቤተሰቡ አባል (እርስዎን ጨምሮ) በአሁኑ ወቅት በሚከተሉት የእርዳታ ፕሮግራሞች ውስጥ ይሳተፋሉ-SNAP ወይም TANF? **አንዱን ይክበቡ ፤** አዎ / አይ

መልሱ **አይ** ከሆነ ወደ **ደረጃ 3** ይሂዱ።

መልሱ **አዎ** ከሆነ ከ 7-12 አሃዝ ያለውን የመለያ ቁጥር ይፃፉ ከዚያም ወደ **ደረጃ 4** ይቀጥሉ። **የኢ.ቢ.ቲ ካርድ ቁጥር አይጠቀሙ።**

የመለያ ቁጥር ፤

ደረጃ 3፤ የቤተሰብ ጠቅላላ ገቢ (በደረጃ 2 ላይ የተሰጠው መልስ 'አዎ' ከሆነ ይህን ደረጃ መሙላት አያስፈልግም።)

የቤተሰቡን አባላት ስም ዘርዝር (የራስህን ጨምር) የወር ገቢ ባይኖርህም። የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል አጠቃላይ ገቢ (ከታክስ በፊት) የአያዳንዱ የገቢ ዓይነት በዶላር (ሣንቲም አይፃፍ)። ምንም ገቢ ከሌለ "0" ቁጥር ፃፍ። "0" ተበሎ ከተፃፈ ወይም በዚህ ክፍል ላይ ምንም ነገር ካልተፃፈ ምንም ገቢ የሌለ መሆኑን እያሰወቁ ነው።

ጠቅላላ ገቢ እና ምን ያህል ጊዜ ያገኛሉ፤ **W** = በሣምንት **E** = በየሁለት ሥምንት **T** = በወር ሁለት ጊዜ **M** = በየወሩ

የቤተሰቡን አባላት ስም ዘርዝር (የመጀመሪያ እና የመጨረሻ)	እድሜ	ከስራ ገቢ	በምን ያህል ጊዜ	የመንግስት እርዳታ / ልጅ ማሳደጊያ / ከቀድሞ የትዳር ጎደኛ የኑሮ መደጐሚያ	በምን ያህል ጊዜ	ጡረታ ከፍያ ሌሎች ገቢዎች	በምን ያህል ጊዜ
ለምሣሌ፤ *John Smith*	35	$ 28000	W E T M (A)	$ 150	W (E) T M A	$ 3000	W E T (M) A
		$	W E T M A	$	W E T M A	$	W E T M A
		$	W E T M A	$	W E T M A	$	W E T M A
		$	W E T M A	$	W E T M A	$	W E T M A
		$	W E T M A	$	W E T M A	$	W E T M A
		$	W E T M A	$	W E T M A	$	W E T M A

ደረጃ 4 ፤ የመገናኛ መረጃና የአዋቂ ሰው ፊርማ

የተሞላውን ቅፅ ለሚከተለው አድራሻ ይላክ ፤ School Nutrition Services, 1340 Braddock Place, Alexandria VA 22314

"በዚህ ቅፅ የተሞላው መረጃ ትክክለኛ መሆኑንና ገቢ በሙሉ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን አረጋግጣለሁ። ይህ መረጃ የተሰጠው ከፌደራል ፈንድ ጋር ተያይዞ መሆኑን አገነዘባለሁ። እንዲሁም የትምህርት ቤቱ ኃላፊዎች መረጃውን ለማጣራት ይችላሉ። ሆን ብየ የተሳሳተ መረጃ ከሰጠሁ ልጆቼ የምግብ አገልግሎት ሊያጡ እንደሚችሉ አረዳለሁ ። እንዲሁም በፌደራልና በስቴት ህግ መሰረት ልከሰስ እንደምችል ተረድቻለሁ።"

ይህን ቅፅ የሞላው አዋቂ ሰው ስም ይፃፍ

ቅፁን የሞላው አዋቂ ሰው ስም ፊርማ X SIGN HERE

የዛሬው ቀን M M D D Y Y

የቤተሰብ አባላት ብዛት (ልጆች እና አዎቂዎች)

ፊርማ የሚፈርመው አዋቂ ሰው ሶሻል ሴክዊሪቲ የመጨረሻው አራት ቁጥር *** - ** -

የሶሻል ሴክዩሪቲ ቁጥር ከሌለ ምልክት ያድርጉ

የመንገድ አድራሻ

የቤት ቁጥር(**Apt #**)

ከተማ

ስቴት

ዚፕ ኮድ

የቤት ወይም የሞባይል ስልክ ቁጥር ( )

የሥራ ስልክ ቁጥር ( )

ኤሚል አድራሻ ይፃፍ

☐ **የትምህርት ቤቱ የተመጣጠነ ምግብ አገልግሎት በዚህ ማመልከቻ ያለውን መረጃ ለሜዲክ አይድና ለሸርጂኒያ የጤና ኢንሹራንስ ፕሮግራም (FAMIS) ለማሳወቅ ይችላል።** ***ይህ መረጃ ወደሌላ እንዳይተላለፍ የሚፈልጉ ከሆነ እዚህ ሣጥን ምልክት***

☐ የእርስዎ ልጅ(ዎች) **ለአካዳሚክ** እና **የኮሚዩኒቲ** አገልግሎቶች ማለትም አትሌቲክ ክፍያ፣ የፈተና መውሰጃ ቫውቸር፣ የጥርስ/አይን ህክምና ፣ የቢጋ እንቅስቃሴዎች ወዘተ...ተጠቃሚነት ብቁ ሊሆን ይችላል። ከዚህ ጎን ባለው ሳጥን ላይ ምልክት በማድረግ የእርስዎን መረጃ ለአካባቢው የጤና እና የትምህርት አገልግሎቶች እንዲሆን ለትምህርት ቤት ኃላፊዎች/ፕሮግራም እንድናካፍል እርስዎ ለእኛ ፈቃድ ሰጥተዎል።

በፈቃደኝነት የሚሞላ

የዘር ወይም የጐሣ ማንነት መግለጫ የልጅዎ ዘር ወይም የጐሣ ማንነት በማመለከት መረጃ እንዲሰጡን እንጠይቃለን። ይህ መረጃ በጣም ጠቃሚ ሲሆን ማህበረሰቡን በተማላ መልክ አገልግሎት የሰጠን መሆኑን ለማረጋገጥ ያስችላል። **በዚህ ክፍል የሚሰጠው መልሰ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሲሆን በልጅዎ ብቁነት በምንም ሁኔታ ተፅእኖ አያሳድርም።**

ጐሣ(አንዱን ይምረጡ።) ☐ ስፖኒሽ ወይም ላቲኖ ☐ ስፖኒሽ ወይም ላቲኖ ያልሆነ

ዘር (አንድ ወይም ከዚያ በላይ) ☐ የአሜሪካን ህንድ ወይም የአላስካ ተወላጅ ☐ ኤዥያ ☐ ጥቁር ወይም የአፍሪካ አሜሪካዊ ☐ የሐዋይ ወይም የፖስፊክ ደሴት ተወላጅ ☐ ነጭ

OFFICE STAFF ONLY - DO NOT Write in this Section

Total Household Size: _____ **Income: $** _____ **W** ___ **E** ___ **T** ___ **M** ___ **A**

Processing Official: _____ **Date:** _____ ☐ Categorical Eligibility Foster SNAP TANF **Approved:** Free ____ Reduced ____ Denied ____

Reason for Denial: Income ____ Incomplete ____ **Reviewing Official:** _____ **Date reviewed:** _____

VERIFICATION SUMMARY: **Date Selected:** **Date Response Due:** **Date of 2nd Notice:** **Date Verification Results Notice Sent:**

Verification Results: No Change | Free to Reduced | Free to Paid | Reduced to Free | Reduced to Paid **Reason for Change:** Income | Household Size | Refused to Cooperate | SNAP/TANF Eligibility

Date: **Verifying Official's Signature:**